# አንበሳ እና አይጥ

አንድ አንበሳ በአንድ ወቅት ከአደን በኂላ በጫካ ውስጥ አረፍ ብሎ ነበር፡፡ ቀኑ ሞቃታማ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት እንቅልፍ ተጫጫኔነውና በዚያው ሽለብ አደረገው ፡፡

እሱ ሽለብ እንዳደረገው አንዲት አይጥ መጣች፡፡ አይጧ ሲጥ ሲጥ እያለች ነበር፡፡ ሲጥ ሲጥ እያለች ልብ ሳትለው አፍንጫው ስር ደረሰች፡፡ በዚህ ጊዜ አንበሳው ካንቀላፋበት ነቃ፡፡ በጣምም ተበሳጨ፡፡ ከዚያም አጉረመረመና አይጧን ሊበላት አፈፍ አደረጋት፡፡

አይጧ ክው ብላ ደነገጠች፡፡ ተንቀጠቀጠች፡፡ በፍርሐት ውስጥ ሆናም ‹‹እባክህ ይቅር በለንኝ›› እያለች ተማጸነው፡፡ ‹‹እባክህ ማረኝ፤ አንድ ቀን ውለታህን እመልሳለሁ›› ስትልም ተለማመጠችው፡፡

አንበሳው  በንቀት እየተመከታት ‹‹ደሞ አንቺ በምን አቅምሽ ነው ውለታ የምትመልሺው?›› አለ፡፡ ከመፍራትዋ የተነሳ መልስ ልትሰጠው አልቻለችም፡፡ አንበሳው ግን አዘነላትና፣ ‹‹በይ ሂጂ፤ ጥፊ ከዚህ›› ብሎ ለቀቃት፡፡

ከጥቂት ቀናት በኂላ አንበሳው በጫካ ውስጥ ምግቡን እየፈለገ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ሳያስበው በአዳኝ መረብ ተያዘ፡፡ ከመረቡ ራሱን ለማላቀቅ ታገለ፡፡ ግን አልቻለም፡፡ ስለዚህ  ለእርዳታ ድምጹን ከፍ አድርጎ ጮኸ፡፡

በዚህ ጊዜ አይጧ ድምፁን ሰምታ  መጣች፡፡ አንበሳው በአዳኙ መረብ ተይዞ ተመለከተች፡፡ ከዚያም የመረቡን ገመድ በስለታም ጥርሶችዋ ቀረጣጥፋ ቆራረጠችው፡፡ አንበሳውም ከመረቡ ነጻ ወጣ፡፡

አይጧም አንበሳውን በመርዳት ውለታዋን ለመመለስ በመቻልዋ ተደሰተች፡፡ ከዚያም እንዲህ አለችው፤ ‹‹አየህ ጌታው አንበሳ! አይጥ እንኳን አንበሳን መርዳት ትችላለች፡፡››

አያችሁ ልጆች፤ የሌሎችን አቅም አቅልሎ መመልከት አይገባም፡፡ ከዚህ ተረት የምንማረው ይህንን ነው፡፡